# ትምህርት 32

1. እግዚአብሔር ፈርዖንንና ሠራዊቱን በቀይ ባሕር ውስጥ ከደመሰሳቸው በኋላ እስራኤላውያንን ወዴት መራቸው?

ሀ- ወደ ምድረ በዳ።

2. ምድረ በዳ ምንድን ው?

ሀ- ምድረ በዳ አሸዋ ብቻ የሚገኝበት ምድር ነው።

3. እግዚአብሔር በምድረ በዳ እየመራቸው ሳለ እስራኤላውያን ምን አደረጉ?

ሀ- እስራኤላውያን ሙሴንና አሮንን ነቀፉ።

4. እስራኤላውያን ሙሴንና አሮንን የነቀፉአቸው ለምን ነበር?

ሀ- ምንም ምግብ ስላልነበራቸው።

5. እስራኤላውያን ምግብ ያጡት በምን ምክንያት ነበር?

ሀ- በምድረ በዳ ምንም ምግብ ባለመኖሩ።

6. ሙሴ በምድረ በዳ ለእስራኤላውያን ምግብ ማግኘት ችሎ ነበር?

ሀ- አልቻለም።

7. እስራኤላውያን በምድረ በዳ ለራሳቸው ምግብ ማግኘት ችለው ነበር?

ሀ- አልቻሉም።

8. ለእስራኤላውያን በምድረ በዳ ምግብ መስጠት የቻለው ማን ብቻ ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር።

9. ሰዎች ባያምኑትም እንኳ፥ እግዚአብሔር የሚረዳቸው ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ስለፈጠረ ነው።

ለ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ስለሚወድ ነው።

ሐ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ማዳን ስለሚፈልግ ነው።

መ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉም ሰው እንዲያምንበት ስለሚፈልግ ነው።

10. እኛ በእግዚአብሔር ካላመንን እግዚአብሔር ያድነናል?

ሀ- አያድነንም።

11. እግዚአብሔር በዚያች ምሽት በምድረ በዳ ለእስራኤላውያን የሰጣቸው ሥጋ ምን ነበር?

ሀ- ድርጭት።

12. እግዚአብሔር ከሰማይ ያወረደላቸውን እንጀራ እስራኤላውያን ምን ብለው ሰየሙት?

ሀ- መና።

13. እግዚአብሔር ሙሴ ውኃን ለማግኘት ምን እንዲያደርግ ነገረው?

ሀ- እግዚአብሔር ሙሴ በበትሩ ዓለቱን እንዲመታው አዘዘው።

14. ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ሊያድነን የሚችለው ማን ብቻ ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ብቻ።

15. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ያዳናቸው እነርሱ በወሰኑት መንገድ ነው?

ሀ- አይደለም።

16. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ያዳናቸው እንዴት ነበር?
ሀ- እግዚአብሔር ራሱ በወሰነው መንገድ ነው።

17. እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ የሚያድነው እንዴት ነው?
ሀ- እግዚአብሔር ራሱ በወሰነው መንገድ ነው።

- ሙሴና እስራኤላውያን የት ነው ያሉት?

- ምድረ በዳ።

- እግዚአብሔር በምድረ በዳም እስራኤላውያንን መምራቱን ቀጥሏል።

ዘጸአት 19፡1

1- በሦስተኛው ወር እስራኤላውያን ግብፅን ለቅቀው በወጡበት በዚያች ዕለት፣ ወደ ሲና ምድረ በዳ መጡ።

- እስራኤላውያን ወዴት መሄድ እንዳለባቸው የወሰነው ማን ነበር?

- እግዚአብሔር።

- እስራኤልን ወዴት መሄድ እንዳለባቸው እግዚአብሔር የወሰነው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም የተሻለውን መንገድ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው።

- ለእስራኤላውያን የተሻለውን መንገድ እግዚአብሔር እንዳወቀላቸው ሁሉ ለሰዎች ሁሉ የተሻለውን መንገድ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- ቀጥሎስ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወዴት መራቸው?

ዘጸአት 19፥2

2- ከራፊዲም ከተነሡ በኋላ፣ ወደ ሲና ምድረ በዳ ገቡ፣ እስራኤልም በዚያ በምድረ በዳው በተራራው ፊት ለፊት ሰፈሩ።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደ ሲና ተራራ መራቸው።

- የሲናን ተራራን ታስታውሱታላችሁ?

- የሲና ተራራ እግዚአብሔር ከሚነድድ ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ ሙሴን የተናገረበት ቦታ ነው።

- እግዚአብሔር ከሚነድድ ቁጥቋጦ ውስጥ ሙሴን ሲያነጋግረው የገባለት ቃል ምን ነበር?

- እግዚአብሔር ሙሴን መልሶ ወደ ሲና ተራራ እንደሚያመጣው ቃል ገብቶለት ነበር።

- እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ሲና ተራራ እንደሚመልሰው የገባውን ቃል ጠብቆአል?

- አዎን።

- ፈርዖን ሙሴን ሊገድለው ቢፈልግም እንኳ እግዚአብሔር ሙሴን ጠበቀው መልሶም ወደ ሲና ተራራ አመጣው።

- እኛ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ሁሉ እናምናለን ምክንያቱም እግዚአብሔር የገባውን ቃል ሁሉ ምንጊዜም ይፈጽማል።

- ሙሴና እስራኤላውያን ወደ ሲና ተራራ በደረሱ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ተራራ ጫፍ ጠራው።

- እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ተራራ ጫፍ የጠራው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር ሙሴን ሊያናግረው ፈለጎ ነው።

ዘጸአት 19፡3-5ሀ

3- ከዚያም ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ወጣ፤ እግዚአብሔርም ከተራራው ጠራውና እንዲህ አለው፤ «ለያዕቆብ ቤት የምትለው ለእስራኤልም ሕዝብ የምትናገረው ይህ ነው፤

4- በግብፅ ላይ ያደረግሁትን እናንተ ራሳችሁ አይታችኋል፣ በንስርም ክንፍ ተሸክሜ ወደ ራሴ እንዴት እንዳመጣኋችሁ።

5- አሁንም በፍጹም ብትታዘዙኝና ቃል ኪዳኔን ብትጠብቁ፣ እነሆ ከአሕዛብ ሁሉ እናንተ የተወደደ ርስቴ ትሆናላችሁ፤ ደግሞም ምድር ሁሉ የእኔ ነው፤ ቅዱስ ሕዝብና የንጉሥ ካህናት ትሆናላችሁ፤' ለእስራኤል የምትነግሩት ይህን ነው።»

- እግዚአብሔር በተራራው ጫፍ ላይ ሙሴን ምን አለው?

- እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ቃል ኪዳን ማድረግ እንደሚፈልግ ነገረው።

- እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ለማድረግ የፈለገው ቃል ኪዳን ምን ነበር?

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን የእርሱን ትእዛዛት ሁሉ ቢጠብቁ እንደሚባርካቸው ተናገረ።

- እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ ባይጠብቁ እግዚአብሔር ምን ያደርጋል?

- ይቀጣቸዋል።

- ሙሴ ከተራራው ወርዶ እግዚአብሔር ምን እንዳለው ለእስራኤልውያን ነገራቸው።

- ከዚያስ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ምን አሉ?

ዘጸአት 19፥7-8

7- ስለዚህ ሙሴ ተመለሰ። የሕዝቡን አለቆች አስጠራ፤ እንዲናገር እግዚአብሔር ያዘዘውን ቃሎች ሁሉ ነገራቸው።

8- ሕዝቡም ሁሉ በአንድ ላይ፣ «እግዚአብሔር ያለውን ነገር ሁሉ እናደርጋለን» ብለው መለሱ፤ ስለዚህ ሙሴ እነርሱ ያሉትን መልሶ ወደ እግዚአብሔር ወሰደ።

- ከዚያስ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ምን አሉ?

- እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ እንደሚያደርጉ ገለጹ።

- እስራኤላውያን ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር አልታዘዝ ይሉ እንደ ነበር አስታውሰዋል?

- አላስታወሱም።

- እስራኤላውያን ፈርዖንና ሠራዊቱ አባርረዋቸው ቀይ ባሕር ድረስ በመጡ ጊዜ እግዚአብሔር ሊያድናቸው እንደሚችል አለማመናቸውን ዘንግተው ነበር።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር በምድረ በዳ ምግብና ውኃ ሊሰጣቸው እንደሚችል አለማመናቸውን ዘንግተው ነበር።

- እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ መጠበቅ እንደሚችሉ አስበው ነበር?

- አዎን።

- እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሁሉ መጠበቅ እንደሚችሉ ያሰቡት ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ትዕቢተኞችና እምቢተኞች ስለ ነበሩ ነው።

- እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ መጠበቅ ችለው ነበር?
- አልቻሉም።

- እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ መጠበቅ ያልቻሉት ለምን ነበር?

- የአዳምና ሔዋን ልጆች ሆነው ስል ተወለዱ ነው።

- የኃጢአት ባሪያዎች ሆነው ስለተወለዱ ነው።

- የሰይጣን ባሪያዎች ሆነው ስለተወለዱ ነው።

- ሰዎች ሁሉ ከአዳምና ሔዋን የተወለዱ ናቸው።
- ሰዎች ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ሆነው ተወልደዋል።
- ሰዎች ሁሉ የሰይጣን ባሪያ ሆነው ተወልደዋል።

- እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ መጠበቅ እንደማይችሉ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር?

- አዎን።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ መጠበቅ እንደማይችሉ እያወቀ ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ማድረግ ለምን ፈለገ?

- እያወቃችሁ በቃሉ ከማይጸና ሰው ጋር ቃል ኪዳን ትገባላችሁ?
- አትገቡም።

- ታዲያ እግዚአብሔር እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ መጠበቅ እንደማይችሉ እያወቀ ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ማድረግ የፈለገው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ቃል ኪዳን የገባው እስራኤላውያንን ሊያስተምራቸው ነበር።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ሊያስተምራቸው የፈለገው ምን ነበር?

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን የእርሱን ትእዛዛት ሁሉ መጠበቅ እንደማይችሉ እንዲያውቁ ሊያስተምራቸው ፈለገ።

- እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ ለመጠበቅ ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም ፈጽሞ አይችሉም።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ መጠበቅ በጭራሽ የማይችሉት በኃጢአት ስለ ተወለዱ መሆኑን ሊያስተምራቸው ፈለገ።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ትእዛዛቱን ሁሉ መጠበቅ በጭራሽ ስለማይችሉ እግዚአብሔር ብቻ ከዘላለም ሞት ሊያድናቸው እንደሚችል ሊያስተምራቸው ፈለገ።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአት ስለ ሠሩ ሁሉም ልጆቻቸው የተወለዱት በኃጢአት ነው።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአት ስለ ሠሩ ሁሉም ልጆቻቸው ኃጢአት በልባቸው አድሮ ነው የተፈጠሩት።

- አዳምና ሔዋን ሰይጣንን ስላዳመጡ ሁሉም ልጆቻቸው የኃጢአት የሞትና የሰይጣን ልጆች ሆነዋል።

- አዳምና ሔዋን ሰይጣንን ስላዳመጡ ሁሉም ልጆቻቸው የኃጢአት የሞትና የሰይጣን ባሪያ ሆነዋል።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ኃጢአታቸውን ማሳየት ፈለገ።
- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ክፋታቸውን ማሳየት ፈለገ።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የኃጢአት ባሪያዎች መሆናቸውን ለማሳየት ፈለገ።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የክፉት ባሪያዎች መሆናቸውን ለማሳየት ፈለገ።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰይጣን ባሪያዎች መሆናቸውን ለማሳየት ፈለገ።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን፥ እነርሱን እንዲያድናቸው ወደ እርሱ ባይጮኹ በኃጢአታቸው ምክንያት እንደሚጠፉ ለማሳየት ፈለገ።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር እንዲያድናቸው ወደ እርሱ ባይጮኹ ሰይጣን እንደሚያጠፋቸው ለማሳየት ፈለገ።

- ከኃጢአት ኃይል ሊያድነን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- ከሞት ኃይል ሊያድነን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- ከሰይጣን ኃይል ሊያድነን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር የገባው ቃል ኪዳን ይህ ነው፡-

- እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ የሚጠብቁ ከሆነ እግዚአብሔር ይባርካቸዋል።

- እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ ባይጠብቁ እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል።

- ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ቀርቦ እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ ለመጠበቅ መስማማታቸውን ሲነግረው፥ እግዚአብሔር ምን አለ?

ዘጸአት 19፥9ሀ & 10-11

9- እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ «ከአንተ ጋር ስነጋገር ሕዝቡ እንዲሰሙኝና እምነታቸውን ምንጊዜም በአንተ ላይ እንዲጥሉ በከባድ ደመና ወደ አንተ እመጣለሁ።»

10- እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ «ወደ ሕዝቡ ሂድና ዛሬና ነገ ቀድሳቸው፤ ልብሳቸውን እንዲያጥቡ አድርግ፤

11- በሦስተኛው ቀን ይዘጋጁ፤ ምክንያቱም በዚያ ቀን በሕዝቡ ፊት እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ይወርዳል።»

- እግዚአብሔር ሙሴን «ወደ ታች ወደ ሲና ተራራው ስለምወርድ ሕዝቡ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ንገራቸው» አለው።

- እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ የሚወርደው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን ለእስራኤላውያን ሊያሳይ ስለፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ እንደሚጠላ ለእስራኤላውያን ሊያሳያቸው ስለፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ ለእስራኤላውያን ሊያሳይ ስለፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር ሙሴን በሲና ተራራ ዙሪያ ወሰን እንዲያደርግ ነገረው።

ዘጸአት 19፥12-13

12- እግዚአብሔር እንዲህ አለ «በተራራው ዙሪያ ለሕዝቡ ወሰን አብጅተህ እንዲህ በላቸው። ወደ ተራራው እንዳትወጡ ወይም ግርጌውን እንዳትነኩ ተጠንቀቁ። ማንም ተራራውን ቢነካ በርግጥ ይሞታል።

13- በድንጋይ ይወገራል ወይም በቀስት ይወጋል። ምንም እጅ በእርሱ ላይ አያርፍም፤ ሰውም ሆነ እንስሳ በሕይወት እንዲኖር አይተውም። ወደ ተራራው መውጣት የሚችሉት ከፍ ባለ ድምፅ መለከት በተነፋ ጊዜ ብቻ ነው።»

- እግዚአብሔር በሲና ተራራ ዙሪያ ወሰን እንዲያደርግ ሙሴን ያዘዘው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር የሲና ተራራን ማንም እንዳይነካው ስለፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር የሲና ተራራን ማንም እንዳይነካው የፈለገው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ይወርድ ስለነበር ነው።

- እስራኤላውያን የሲና ተራራን ቢነኩት ምን ይደርስባቸዋል?
- ይሞታሉ።

- እስራኤላውያን የሲናን ተራራ ከነኩ የሚሞቱት ለምንድን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር በተራራው ላይ ይወርድ ስለነበር ነው።
- ምክንያቱም እግዚአብሔር ቅዱስ ስልሆነ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ስለሚጠላ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት ስለሚቀጣ ነው።

- በሦስተኛው ቀን ማለዳ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ወረደ።

ዘጸአት 19፡16-18

16- በሦስተኛው ቀን ጧት ከባድ ደመና በተራራው ላይ ሆኖ ነጐድጓድና መብረቅ እንዲሁም ታላቅ የቀንደ መለከት ድምፅ ነበር፤ በሰፈሩ ያሉት ሁሉ ተንቀጠቀጡ።

17- ከዚያም ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ሕዝቡን ከሰፈር ይዞ ወጣ፤ ከተራራውም ግርጌ ቆሙ።

18- የሲና ተራራ፣ እግዚአብሔር በእሳት ስለ ወረደበት፣ በጢስ ተሸፍኖ ነበር። ጢሱ ከምድጃ እንደሚወጣ ጢስ ወደ ላይ ተትጐለጐለ። ተራራውም በሙሉ ኃይል ተናወጠ።

- እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ወረደ።

- ነጐድጓድም በተራራ አጠገብ ሰማዩን አናወጠው።

- መብረቅ በተራራው ዙሪያ የነበረውን አየር ሞላው።

- ጥቅጥቅ ያለ ጢስ ተራራውን በሞላ ሸፈነው።

- ከፍተኛ የመለከት ድምፅ ተሰማ።

- ተራራው በሙሉ በከፍተኛ ሁኔታ ተናወጠ።

- እግዚአብሔር በተራራው ላይ በእሳት ወረደ።

- እስራኤላውያን ፈርተው ነበር?

- እጅግ በጣም ፈርተው ነበር።

- ነጐድጓድ፥ መብረቅ፥ ጢስና እሳት የምን ምልክቶች ነበሩ?

- እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን የሚያመለክቱ ነበሩ።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ እንደሚጠላ የሚያመለክቱ ነበሩ።
- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ የሚያመለክቱ ነበሩ።

- በኖኅ ዘመን እግዚአብሔር የሕዝቡን ኃጢአት በሞት ቀጥቷል።

- በሰዶምና በገሞራ ዘመን እግዚአብሔር የሕዝቡን ኃጢአት በሞት ቀጥቷል።

- በፈርዖን ዘመን እግዚአብሔር የሕዝቡን ኃጢአት በሞት ቀጥቷል።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት ይቀጣል።

- እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ወርዶ ሙሴን ወደ ተራራ ጫፍ ጠራው።

ዘጸአት 19፡20-25

20- እግዚአብሔር በሲና ተራራ ጫፍ ወረደ፤ ሙሴን ወደ ተራራው ጠራው፤ ሙሴም ወጣ።

21- እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤ «ሕዝቡ እግዚአብሔርን ለማየት በመጣደፍ ብዙዎቹ እንዳይጠፉ ውረድና አስጠንቅቃቸው።

22- ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡት ካሕናት እንኳ፣ ራሳቸውን መቀደስ አለባቸው። አለዚያ እግዚአብሔር ቁጣውን ያወርድባቸዋል።»

23- ሙሴ እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፤ «ሕዝቡ ወደ ሲና ተራራ ሊወጡ አይችሉም፤ ምክንያቱም አንተ ራስህ፣ ‹በተራራው ዙሪያ ወሰን አድርግ፤ የተቀደሰም በማድረግ ለየው› በማለት አስጠቅቀኸናልና።

24- እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፤ «ውረድና አሮንን ከአንተ ጋር ይዘኸው ውጣ፤ ካሕናቱና ሕዝቡ ግን ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት መጣደፍ የለባቸውም፣ አለዚያ እርሱ ቁጣውን ያወርድባቸዋል።»

25- ስለዚህ ሙሴ ወደ ሕዝቡ ወርዶ ነገራቸው።

- እግዚአብሔር ሙሴን ሕዝቡ የሲና ተራራን ቢነኩ እንደሚሞቱ ነገረው።

- እግዚአብሔር ሙሴ ወደ ተራራው ላይ እንዲወጣ የፈቀደለት ለምን ነበር?

- ሙሴ የአዳምና የሔዋን ልጅ አይደለም?
- ነው።

- ሙሴ በኃጢአት አልተወለደም?
- ተወልዷል።

- ታዲያ ሙሴ ወደ ተራራው ላይ እንዲወጣ እግዚአብሔር ለምን ፈቀደለት?

- ምክንያቱም ሙሴ በእግዚአብሔር ስላመነ ነው።

- ሙሴ ወደ እግዚአብሔር የመጣው በእግዚአብሔር መንገድ ነበር።

- ሙሴ ወደ እግዚአብሔር የመጣው እግዚአብሔር ባሳየው መንገድ ነበር።

- እግዚአብሔር ሙሴን የእርሱ መልእክተኛ እንዲሆን መረጠው።

- እግዚአብሔር ሙሴ መልእክቱን ለእስራኤላውያን እንዲያደርስለት መረጠው።

- እስራኤላውያን ሙሴ የሚለውን አንሰማም ካሉ እግዚአብሔርን የሚለውን እምቢ ብለዋል ማለት ነበር።

- የእግዚአብሔር መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም ሰዎች የእግዚአብሔር መልእክት ነው።

- እኛ በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን መልእክት ለመስማት ካልፈለግን እግዚአብሔርን ለመስማት አልፈለግንም ማለት ነው።

- እግዚአብሔርን አንሰማም ካልን እግዚአብሔር ለዘለዓለም ይቀጣናል።

- በሚቀጥለው ትምህርት እግዚአብሔር ለእስራኤላውያንና ለሰዎች ሁሉ ስለ ሰጠው ትእዛዛት እንማራለን።